

## ቇ31-1ቈ

# ከፍትወት ወጥመድ እንሸሽ

## ወድቀን ከማልቀስ አስቀድመን እንጠንቀቅ

ጊዜው ከ40 ዓመት በፊት ይሆናል አንዳንዶቻችን በምሳ ሰዓት ቤተ ክርስቲያን እየሄድን እንጸልይ ነበር። ሁሉም እንደተመቸው የሚያደርገው የጸሎት ጊዜ እንጂ ቤተ ክርስቲያን የምታዘጋጀው የጸሎት ፕሮግራም አልነበረም። አንድ ቀን እንደተለመደው ለመጸለይ እኔም አንድ ጥግ ቦታ ይዤ ተንበረከክሁ። ጥቂት እንደጸለይኩ የአንዲት እህት ለቅሶና ጸሎት የራሴን ጸሎት አስረሳኝ። ስቅስቅ እያለች ስታለቅስ ልቤ ተነካ። አንዳንድ “ካላለቀሱ ያልተባረኩ” የሚመስላቸው ሰዎች የሚጨምቁት እንባ የሚያሰሙት የለቅሶ ዓይነት አልነበረም። ይሄኛው ለቅሶና እንባ ከእውነተኛ አዕምሮ ከተጨነቀ ልብ የወጣ ስለነበረ ልቤን በሃዘን ሞላው። “ምን ሆና ይሆን? ምን ክፉ ነገር ደርሶባት ይሆን? ከእግዚአብሔር በዚህ ሰዓት የምትጠይቀው ምን ይሆን?” እያልኩ እራሴን እጠይቅ ነበር።

የዚያች እህት ለቅሶ ስለ አስጨንቀኝ ጸሎቴን አቋርጬ ማንነቷን ለማወቅ ዓይኔን ከፍቼ ስመለከት በክርስትና ሕይወቷ ብርቱ ናቸው ከምላቸው እህቶች መካከል አንዷ የነበረች ቤተ ክርስትያናችን ውስጥ ትልቅ አገልግሎት የነበራት እህት መሆኗን ተረዳሁ። ልቤ ስለ እርሷ በሃዘን ስለተሞላ እጄን ጭኗ ልጸልይላት ያቺ እህት ወደ ተንበረከከችበት ሥፍራ ሄድኩ። “ለምንድነው እንደዚህ የምታለቅሽው” ጌታ ምን እንዲያደርግልሽ ትፈልጊያለሽ?” ብዬ ሳልጠይቃት የልቧን ጭንቀት ለሚያወቀው ጌታ ሁሉን ትቼ እጄን ጭኜ ለዚያች እህት መጸለይ ጀመርኩ። “ፍላጎቷን አንተ ታወቃለህና አሟላላት” እያልኩ ከልቤ ጸለይኩላት።

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ያቺ እህት ሳታገባ ያረገዘች መሆኗን ሰማሁ። ሁኔታው አስደነገጠኝ እንዲሁም አሳዘነኝ። “ለካስ ያኔ እንደዚያ ስቅስቅ ብላ እያለቀሰች ትጸልይ የነበረው እርግዝናዋ እንዲጠፋላት ነበር?” የሚል ጥያቄ በውስጤ ተፈጠረ። ያቺ እህት ምንም ያህል ስቅስቅ እያለች በማልቀስ ከልቧ ብትጸልይም የምትፈልገውን ዓይነት መልስ ከእግዚአብሔር ማግኘት አልቻለችም። እግዚአብሔር እርሷ የምትፈልገውን ዓይንት መልስ መስጠት አያቅተውም ነበር። ይሁን እንጂ፥ ኃጢአት ዋጋ ያስከፍላልና ይበልጥ የእግዚአብሔርን ይቅርታና ፍቅር በመኅዳት ውስጥ አልፋ እንድትማር ስለፈለገ ይሆናል።

## ኃጢአት መገለጡ አይቀርም

እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ይውደደው እንጂ ኃጢአትን ደብቆና ሸፍኖ ማሳለፍ ባህሪው አይደለም። ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች እንኳን በኃጢአት ሲወድቁ ተሸፋፍነው እንዲታለፉ ካላደረገ እኔና እናንተንም አያልፈንም። ሁኔታው ከተፈጸመ በኋላ ሊሆን ያለው እንዳይሆን ከመጸለይ ይለቅ በቅድሚያ እራሳችንን መቆጣጠርን መማር ይጠቅመናል። ኃጢአት ዋጋ ያስከፍላልና፥ ያቺ እህትና ያስረገዛት ሰው ከቤተ ክርስቲያን እንዲርቁ አደረጋቸው። እኛም ያኔ

የወደቀውን ሰው ደግፈን እንደገና ወደ እግዚአብሔር ይቅርታና ፍቅር በማስጠጋት ፈንታ ከወደቀበት ሥፍራ እንዳይነሳ መልሰን ድንጋይ ወርዋሪዎች ስለ ነበርን እነዚያ ወገኖች ለብዙ ዓመት ከጌታ ቤት ርቀው ሄዱ። የእነዚህ ሁለት ወጣቶች የተደበቀ ሕይወት ይገለጽ እንጂ በተመሳሳይ ሕይወት ውስጥ አልፈው ሳይታወቅባቸው ያለፉ ወይንም ኃጢአታቸው እንዳይታወቅ አጣዳፊ ሠርግ በማድረግ ሁኔታው ተሸፍኖላቸው ያለፉ ሰዎች ምን ይህል እንደ ሆኑ ቤታቸው ይቁጠረው። በኢትዮጵያውያን አማኞች መካከል በአሁኑ ጊዜ ሰይጣን የረቀቀ ሥራውን የሚያካሂደው አንደኛ፥ በክርስቲያኖች መካከል የቡድን መንፈስን እየፈጠረ በመከፋፈልና በመለያየት ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ በሥጋ ፍትወት ብዙዎችን እየወጋ በመጣል ነው። ከየሥፍራው በየጊዜው ብዙ የተለያዩ ደብዳቤዎች ይደርሱናል። ከነዚህ ደብዳቤዎች መካከል አንዳንዶቹ ክርስቲያኖች በሥጋቸው የሚገጥማቸውን ችግር እየዘረዘሩ ምክር ሀሳብና ጸሎት የሚጠይቁ ናቸው። አንዳንዶቹም በንስሃ መልክ “በተደጋጋሚ በሥጋ ፈተና ወደቅሁ ሥጋዬን አሸንፌ ብርቱ ክርስቲያን ሆኜ ለመኖር እፈልጋለሁ ግን አቃተኛ እባካችሁን መመሪያ ስጡኝ አስተምሩኝ” ብለው የሚጠይቁን ብዙዎች ናቸው።

እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ በሥጋ ፍትወት እየተወጉ የሚወድቁ መንፈሳዊ መሪዎች ቁጥር በየጊዜው እያጨመረ ነው። የታወቀው ወንጌላዊ ጂሚ ስዋገርት በድጋሚ ካሊፎርኒያ ውስጥ ከሴተኛ አዳሪ ጋር በመያዙ በመፍረድ ፈንታ በነገሩ ትኩረት በመስጠት ይህን ትምህርት ለኢዮጵያውያን አማኞች ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። እንደ ጂሚ ስዋገርት አይያዙ እንጂ ቤተክርስቲያን እየተመላለሱ እያገለገሉ በተምሳሳይ ኃጢአት ውስጥ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ምን ያህል ይሆኑ? ይህ ትምህርት ጠቃሚነቱ ለደካማዎች ብቻ ሳይሆን “እኔ አግብቻለሁ፤ እኔ ብርቱ ነኝ የሥጋ ፈተና የለብኝም፣ እኔን አይመለከተኝም” የምንለውንም ሁሉ ይጨምራል። “ማንም ቆሜአለሁ የሚል፥ እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ” ይላል (1ኛ ቆሮ. 10፥12)።

## ፍትወት ለመፈሳዊ ሕይወት መርዝ ነው።

የሥጋ ፍትወት ኃይል በዓለም ውስጥ ያሉት የጦር ኃይሎች በአንድ ላይ ሆነው ከሚኖራቸው ኃይልና ጉልበት ይበልጥ አለው። በጦርነት ካለቁት ሰዎች ይበልጥ በሥጋ ፍትወት ምክንያት ያለቁት ይበልጣሉ። በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች በየዓመቱ በሥጋ ፍትወት ምክንያት ይሞታሉ። የመሬት መንቀጥቀጥና ጎርፍ እንዲሁም ኃይለኛ አውሎ ነፋስ ካፈረሳቸው ቤቶች ይልቅ በሥጋ ፍትወት ምክንያት የፈርሱት ቤቶች ይበልጣሉ። የሥጋ ፍወትወት ማንንም አይመርጥም። ሀብታሙንም ሆነ ድሀውን፣ የተማረውንም ሆነ ያልተማረውን፣ በትልቅ ሥልጣን ላይ ያለውንም ሆነ የቀን ሠራተኛውን፣ ወጣቱንም ሆነ አዛውንቱን፣ ብርቱውንም ሆነ ደካማውን፣ ያገባውንም ሆነ ያላገባውን ይደርፍራል። በሥጋ ፍትወት ምክንያት ሚስቶቻውን ያጡ ባሎች እንዲሁም ባሎቻቸውን ያጡ ሚስቶች ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆች ጥቂቶች አይደሉም። የሥጋ ፍትወት በግልጽ ቶሎ የማይታይ በመሆኑ ብዙዎች አደገኛነቱን አይገነዘቡም።

የሥጋ ፍትወት ቦታ አይመርጥም። በየአደባባዩ፣ በየቤቱ፣ በየመሥሪያ ቤቱ፣ በየፋብሪካው፣ በየቢሮው፣ በባህርም ሆነ በዓየር ይገኛል። በሰዎች ልጆች ላይ ውርደት በሽታን ሞትን ያመጣል። ለሰዎች ጥቂትና ጊዜያዊ ደስታን ከሰጠ በኋላ ያላቸውን አውደሞ ሰባብሮ ለወደፊት የሚሆናቸው ምንም ነገር ሳይተውላቸው ባዶ እጃቸውን ያስቀራቸዋል። ዲትሪሽ ባንሆፈር ጀርመናዊ የሥነ-መለኮት ሊቅ ብርቱ ክርስቲያን ጌታውን የሚወድና የሚከተል ሰው ነበር። በእምነቱ ምክንያት “ብላክ ጋርድ” እየተባለ በሚጠራ በአንዱ በናዚ ጭፍራ በ39 ዓመቱ በአደባባይ ተሰቅሎ ሞተ። ባንሆፈር በሥጋው ይሙት እንጂ ሥራው አልሞተም። እርሱ

የጻፋቸው ጽሁፎች ለብዙ ዘመናት ብዙዎችን እየበረኩ ናቸው። ባንሆፌር ስለ ፈተና ስለ ሥጋ ፍትወት ሲጽፍ እንዲህ ይላል።

"በሁላችንም ውስጣዊ ሕይወት ውስጥ የተኛ የሚመስል ኃይለኛና ፈጣን የሆነ ዝንባሌ አለ። ማንም ሊገታው ወይንም ሊያቆመው በማይችለው ኃይል ሥጋን ጨምድዶ ይይዛል። ፍጹም የማይታይ ይሁን እንጂ ሲነሳ እንደሚንቦገቦግ እሳት በኃይል ይነዳል። ሰው በውስጡ ያለው የሥጋ ፍትወት ለማደግና በልጦ ለመታየት ያለው ጥማት ሌላውን ለመበቀል ያለው ኃይል የዝና የአምባገነንነት ጥማትና የገንዘብ ፍላጎት ፍጹም የሚስተካከለው ኃይል የለም። ሰው በእግዚአብሔር ላይ ያለውን ደስታ ያጠፋና የሰው ደስታ በተፈጣሪ ነገር ላይ እንዲሆን ያደርጋል። ይህ ስሜት በሰው ሕይወት ውስጥ ሲገነፍል የእግዚአብሔር መኖር እውነት ሆኖ አይታየውም። እውነት ሆኖ የሚታየው በዙሪያው የሚያየውና ሰይጣን ብቻ ነው። እዚህ ላይ ሰው እግዚአብሔር እንዲጠላ ሰይጣን አያደርግም፤ የሚያደርገው እግዚአብሔርን እንዲረሳ ነው። በሰው ሕይወት የሥጋ ፍትወት ሲነድ አዕምሮውንና ፈቃዱን ያጨልማል። እንዲሁም ትክክለኛ ሚዛንና አስተያየት እንዳይኖረው አዕምሮውን ይሠረቃል" ይላል።

ብዙዎች አምነው አይቀበሉት እንጂ ሥጋ ለባሽ የሆነ ሰው ሁሉ የሥጋ ፍትወት (lust) ግፊት (ፈተና) አለበት። ፈተናን "እምቢ" ለማለት ወሳኙ ግን እያንዳንዱ ሰው ነው። በሥጋ ፍትወት የሚመራ ሰው አስተያየት የጎደለው ሰው እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። "የምንዝር ተግባር የሚፈጽም ሰው ግን ማስተዋል የጎደለው ነው፤ ሕይወቱንም በከንቱ ያጠፋል። ውርደትና ድብደባ ይደርስበታል፤ ሁልጊዜም እንደ ተዋረደ ይኖራል" ይላል (ምሳሌ 6፥32-33)። እግዚአብሔር የሩካቤ ሥጋ ፍላጎት በሰው ውስጥ እንዲኖር አድርጎ ስለፈጠረው በአገባቡ ከተፈጸመ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት በመሠረቱ ኃጢአት አይደለም። ሰው ደስታን ከሚያገኝባቸው ነገሮች መካከል አንዱ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ነው። ይህንን ፍላጎት በሰው ሕይወት ውስጥ በማድረጉ እግዚአብሔር አልተሳሳተም። ችግሩ ግን ሰው ከመስመር ወጥቶ ሲጠቀምበት ብቻ ነው። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በጋብቻ የተጣሠሩ ባልና ሚስት የሚፈጽሙት የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት የተቀደሰ ነው። በጋብቻ ሕይወት ውስጥ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት አስፈላጊ በመሆኑ፣ እራሱ ያላገባም ቢሆን ጳውሎስ "እርስ ባርሳችሁ አትከላከሉ" እያለ የተጋቡትን ይመክራል (1ኛ ቆሮ. 7፥3-5)። ከጋብቻ ውጪ የሚሆነውን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ግን መጽሐፍ ቅዱስ ይቃወማል (1ኛ ቆሮ 6፥15-20 1 ተሰሎንቄ 4፥2-8)። ሌላው ቀርቶ መስመር የለቀቀ ምኞት እንኳን ኃጢአት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ማቴ. 5፥27-28)። የብዙዎች ችግር የዓይን አዕምሮት፣ የሥጋ ፍትወት ኃጢአት መሆኑን አለማወቅ አይደለም። ችግሩ ከዚህ ሕይወትን ገርስሶ ከሚጥል፣ ከሚያዋርድ ቤትንና ንብረትን ከሚያፈርስ፣ ከሚወደው ከአምላኩ ጋር ከሚለያየው፣ መርዘኛ ከሆነው የሥጋ ፍትወት መሸሽ የሚቻልበት መንገድ አለማወቁ ላይ ነው።

## የሥጋ ፍትወት የሰይጣን መሣሪያ ነው

ስለሚያጋጥሙን ልዩ ልዩ ፈተናዎች ከማወቃችን በፊት ስለፈታኛችን ጠባይና ባህሪ እንወቅ። ስለ ፈታኙ ጠባይና አቋም መጀመሪያ የተገለጸው በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ላይ ነው። "እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠራቸው አራዊት ሁሉ እባብ እጅግ ተንኮለኛ ነበር" (ዘፍ. 3፥1) ይላል። እባብ ተብሎ የተተረጎመው ቃል "ናካሽ" ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ነው። "ናካሽ" ትክክለኛ ትርጉሙ እባብ ማለት ሳይሆን "የሚያንጸባረቀው አንጸብራቂው" ማለት ነው። ስለዚህ "እባብ" በሚለው ቃል "አንጸባራቂው" የሚለውን ቃል ተክተን ብናነበው ጥቅሱ "እግዚአብሔር ከፈጠራቸው አራዊት ሁሉ "አንጸባራቂው" እጅግ ተንኮለኛ ነበር" የሚል ይሆናል። ይህ ቃል

ለአንዳንዶቻችን “እባብ እንዴት ይናገራል?” ለሚለው ጥያቄያችን መልስ ይሆነናል። “እባብ” “ለአንጸባራቂው” ምሳሌ ነው። በዘፍጥረት 3 ላይ ለሄዋን የተገለጸላት እባብ ሳይሆን “አንጸባራቂው” ሰይጣን ነው። ጳውሎስ ሲገልጸው “የብርሃን መልአክ” ይለዋል (2ኛ ቆሮ. 11፥14)። ተንኮለኛነቱ በግልጽ የታወቀው ገና ከመጀመሪያው “በሄዋን ስሜት” ላይ መጫወት ሲጀምር ነው። ሰይጣን ወደ ሰው ሲመጣ ቀንድና ጭራውን እያሳየ “መጣሁብህ ሰይጣን ነኝ” እያለ አይመጣም። ማንነቱን አሳውቆ ወደ ሰው ቢመጣ ኖሮ ማንንም ባልተታለለትም ነበር።

**<u>ሰይጣን የሚጠቀምበት ዘዴ ምንድነው?</u>**

ሰይጣን “የብርሃን መልአክ” ብቻ ሆኖ ወደ ሰው አይመጣም። “ሰይጣን እንደሚያጓራ አንበሳ በዙሪያችን ይዞራል” ይለዋል መጽሐፍ ቅዱስ። የአንበሳን ጉልበትና ኃይልን ይዞ ሰውን በበሽታ በሃዘን በመከራ ሊመታ ይቻላል። ኢዮብ በዚህ ኃይል ተምትቷል። ጳውሎስም “ስለ ስጋው መወጊያ” ሲናገር “የሰይጣን መልአክተኛ ተሰጠኝ” በማለት የሰይጣንን ኃይል ይገልጻል። እንዲሁም እንደ አንበሳ በማንጓራት በልባችን ውስጥ የፍርሃትን መንፈስ ይረጫል። እያንዳንዱ ሰው የሚፈተነው በገዛ ራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው። ከዚህ በኋላ ምኞት ስትጸንስ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ስታድግ ሞትን ትወልዳለች” በማለት ተደጋጋሚ የሆነውን የሰይጣንን ታክቲክ (ዘዴ) ያዕቆብ ይገልጸዋል (ያዕቆብ 1፥14-15)። በሔዋን ላይ የተጠቀመው ዘዴ ይሄን ዓይነት ነበር፤ ዛሬም በእኛ ላይ የሚጠቀመው ዘዴ ይሄንኑ ዓይነት ነው።

ሀ) መጀመሪያ ስሜታችንን በመቀስቀስ አዕምሮአችን እንዳያስብ የማሰብ ችሎታችንን በመዝጋት ነው። ያዕቆብ “ሰው የሚፈተነው በገዛ ራሱ ምኞት ሲሳብ” ነው ያለው ለዚህ ነው። ስሜቱን ከቀሰቀሰ በኋላ ለዚያ ልክ ላልሆነ ነገር ፍጹም እንዲራብ ያደርገዋል።

ለ) ሁለተኛ ምኞቱን በሥራ እንዲተረጉም ያባብለዋል። እውነት ያልሆነ ምክንያት ይሰጠዋል። ሔዋንን “እንደ እግዚአብሔር ክፉውንና ደጉን ታውቃላችሁ” አላት። ያዕቆብ “ምኞት ስትጸንስ ኃጢአትን ትወልዳለች” ያለው ሰው ምኞቱን በሥራ ሲተረጉመው ነው።

ሐ) ሦስተኛና የመጨረሻው ደረጃ ሰይጣን የሚፈልገውን ዓላማ ሲነካ ነው። ያም፥ ለሰው ልጅ “ሞትን” መስጠት ነው። “ኃጢአትም ስታድግ ሞትን ትወልዳለች” (የዕቆብ 1፥15)። ሞት በአለበት አካባቢ ጠላትን አሸንፎ በድል አድራጊነት መመለስ ምን ያህል ትልቅ ደስታና ዕድል ነው! ሐዋርያው ጳውሎስ “በዚህ ሁሉ በእርሱ ከአሸናፊዎች ሁሉ እንበልጣለን” ይላል (ሮሜ 8፥37)። “በዚህ ሁሉ” የሚለው ጳውሎስ በልዩ ልዩ ፈተናዎች ማለቱ ነው። “ከአሸናፊዎች ሁሉ እንበልጣለን” ሲል ደግሞ ምን ማለቱ ይሆን?

……………………………………………………………………………

**በሚቀጥለው ክፍል እንክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**